# እንደ መንግስት እናስብ

ዜጎች በየትኛውም ማህበረሰብ በቡድን ሆነ በተናጠል ያገባናል በሚልዋቸው በመብቶቻቸውና ጥቅሞቻቸው ላይ የተቃጡ የመሰልዋቸው የመንግስት ፖሊሲዮችና የልማት አጀንዳዎች የመቃወም ሆነ የመደገፍ ህገ መንግሰታዊ መብት ነው፡፡ የአገሪትዋ የወር ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ የሰነበትው በኦሮምያ የሰነበተው ተቃውሞ በዋናነት እንደምክንያት ሆኖ ሊቀርብ የሚችለው በመላው አገሪቱ እንደ አረም የተንሰራፋ የመልካም አስተዳደር እጦት ቢሆንም እንደ ገፊ ምክንያቶች ሊጠቀሱ የሚችሉና ተገቢ ዋጋ ሊሰጣቸው የሚገባ የአዲስ አበባና ፊንፊኔ ዙርያ የኦሮምያ ልዩ ዘኖች የተቀናጀ ማስትር ፕላን፤የኦሮምያ ከተሞችን እንደገና ለማቋቋም ተሻሽሎ የወጣው አዋጅና ለልማት ተነሺ ህብረተሰብ ጉዳይ (በዋናነት አርሳደሩን ይመለከታል) የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**የአዲስ አበባና ፊንፊኔ ዙርያ የኦሮመምያ ልዩ ዞኖች የተቀናጀ ማስትር ፕላን፤** እንደ አጀንዳ ሆኖ መነሳት የጀመረው በ2006 ዓ.ም ሁለቱ አጎራባት ክልሎች የኦሮምያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትና የአዲስ አበባ መስተዳድ በባለሞያዎች አጥንተው ባቀረቡት ረቂቅ ሲሆን በወቅቱም እንዳሁኑ በስፋትና በወስደው ግዜ የአሁኑን ባያክልም በተነሳው ተቃውሞ መጠነኛ የሆነ ጉዳት በሰው ሂወትና በንብረት ላይ ደርሷል፡፡መንግስት ከዚሁ ክስተት በሀላ የተረቀቀውን ፕላን ፖለቲካዊም ሆነ ህጋዊ መሠረት ያደረግ ውሳኔ ሳይሠጥበት እንደተንጠለጠለ ወቅታዊ ባላቸው የልማት አጀንዳዎች ተጠመድምጄ ከረምኩኝ ብሎናል፡፡

የአሁኖቹ መነሻህሳቦች የያኔውም ግዜ ጥያቂዎች የነበሩና መንግስት በወቅቱ ተገቢ መልስ ሳይሰጥ በመቅረቱ ተዳፍነው በይደር የቆዩ ናቸው፡፡ ምን ጊዜም  ቢሆን የኢትዮጵያ ልማትና እድገት የማይዋጥላቸው የውስጥ እና የውጪ ሀይሎች የህዝቡ የተዳፈነ ጥያቄ ተመልሶ የሚመጣበትን መንገድና መላ ለዓመታት ሲያምጡ የከረሙ መሆናቸው አሁን ያየነው ግርግርና ብጥብጥ ሁነኝ ማሳያ ነው፡፡ መንግስት ማስተር ፕላኑን በተመለከተ ከህዝቡ ጋር ቀጥተኛ ውይይት በማድረግ ግልጽንተ መፍጠር ሲገባው ጥያቄው የጥቂቶችና ብለም የጸረሰላም ሀይሎች ነው በሚል ሂሳባዊ ስሌት ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩርተ ሳይሰጥ በመቅረቱ ሁለተና ዙር ግርግርና ብጥብጥ በመጠኑም ቢሆን ለውድመት በዳረገው የሰው ሂወትና ንብረት በማሳደግ ትልቅ አጀንዳ ለመሆን በቅቷል፡፡

በዚት ረገድ መንግስት ህዝቡን ከማሳመንና ግልጽነት ከመፍጥር አንጻር ጸረሰላም ሀይሎቹ ከሄዱት ርቀትና ልፋት መወዳደር ባለመቻሉ ህዝቡ ባበጁለት የጥፋት አርጅን ለመፍሰስ ተገዷል፡፡ የማስተር ፕላኑ መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳብ በልማት የመተሳሰር የመሰረተልማቶች የማቀናጀት እንጂ የአስተዳዳር ማቀላቀልም ሆነ አዲስ አበባ የማስፋፋት አጀንዳ ሊኖሮው አይችልም፡፡ ምክንያቱ የአዲስ አባባ መስተዳደር ሆነ የኦሮምያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሕገ መንግስቱ የተዋቀሩና የድንበር ወሰናቸው ላይ ሰፋ ላይ ጠብብ ተወስኖ ያለቀለት ጉዳይ ስለሆነ፡፡ ግርግር ናፋቂዎቹ የውስጥና የውጭ ሀይሎች እንደ ነገሩን ጉዳዩ አዲስ አበባ የግዛት ወሰን የማስፋፍት አጀንዳ የሆነ እንደሆነ በአገሪትዋ የሚገኙ ብሔር ብሔረሶችና ሕዝቦች ተወያይተው ያጽደቁትን ሕገ መንግስተ በጀርባቸውና ያለ እውቅናቸው ለማሻሻል የተፈጸመ ደባ እንጂ በኦሮምያ ላይ ብቻ የተቃጣ አደጋ ተብሎ ሊፈረጅ አይችልም፡፡ ሕገ መንግስቱ የማሻሻል

ስልጣን ደግሞ በሁለት ክለልሎች በሚደረግ ስመምነት የሚፈጸም ጉዳይ ሳይን የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተወያይተው የሚፈጽም ትልቅ አጀንዳ ነው፡፡

በመርህ ደረጃ በየትኛውም ዓለም ቢሆን እምቢ ለልማት የሚል ህዝብ ሊኖር እንደማይችል የተረጋጋጠ ቢሆንም ልማትም ቢሆን የትኛውንም ጥቅም ሊያመጣ መቻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ህዝቡ የልማቱ ባለቤት እስካልተደረገ ድረስ ልማቱን የተሳሳተ ምስል በመስጥት አገር በማተራመስ ስማቸውን በታሪክ እንዲጻፍላቸው የሚሹ ወገኖች ለእኩይ ተግባራቸው መጠቀምያ ሊያደርጉት እንደሚችሉ እየታየ ያለውን ሁከትና ግርግር ሁነኛ ማሳያ መሆኑ የሚያስማማን ጉዳይ ነው፡፡ መንግስት ግልጽነት ከመፍጠር አኳያ ሊሄድ ይገባው ከነበረው ርቀት አለመሄዱ ማመኑ በጎ ቢሆንም ከዚሁ ጎን ለጎን ሲደረሩ የነበሩት ምክንያቶች እንደሰበብ ከመቆጠር ውጪ አላፊ አግዳሚ በሚገባው መልኩ ለይስሙላህ የተነገሩ ነገሮች በመሆናቸው እኔ ቅር ተሰኝቸባቸዋለው፡፡ ከተሰጡት ሰበበ አስባቦች ጥቂቶቹ አንዳንዶቹ መንግስት በግልጽ ባያቀርባቸውም ከአንዳንድ ለመንግስት ቅርላቸውና የመንግስት ልሳኖች የተነገሩ ናቸው፡፡ ረቂቅ ስለነበረ ፤ ከ2006 ዓ.ም ተቃውሞ በሀላ እንዲቆም ስለተደረገ ፤ በኦሮምያና በአዲስ አበባ መስተዳደር ምክር ቤት ስላልጸደቀ ፤ አዲስ መንግስት ከተቋቋመ ገና የወራት እድሜ ያስቆጠረ በመሆኑ ወዘተርፈ፡፡ እኔ እስኪገባኝ ድረስ ይህ መንግስት የስልጣን ማማ ላይ ከወጣ እኖሆ 24 (ሀያ አራት ) ዓመት አልፎታል፡፡ ነገር ግን ምርጫ ባሸነፈ ቁጥር የእድሜውን አቆጣጥ እንዳዲስ እየጀመረ የእድሜውን ጣርያ 5 ዓምት ላይ በማስቀመጥ ህዝብ መርጦ ወደ ስልጣን ከመጣው 3 ወር ነው ቅብርጥሴ ምንንጥሴ እያለ ራሱን አሞኝቶ ህዝብን ለማሞኘት በመሞከር ጊዜውን ባያባክን ጥሩ ይመስለኛል፡፡ ይህ አሁን እያየነው ያለነው ችግር እኮ በሶስት ወር ተዘርቶ የበቀለ አረም ሳይሆን በኢህአዴግ የ24 ዓመታት አገዛዝ መፍትሄ ሳይሰጣቸው ተወዝፈው  ሲንከባለሉ የመጡ የህዝብ ብሶት የወለደው ችግር ነው፡፡ አሁን ለመንግስት የሚበጀው የተነሳውን ሕገ መንግስታዊ ጥያቄ ሕገ መንግስቱ በሚፈቅደው ቁመት እና ስፋት ልክ ተወያይቶ በጋር መፍትሄ መፈለግ ነው፡፡ ይህ ሳሆን ቀርቶ እንደ በፊቱ መንግስት እዚጋ ቅድምያ ስሰጥ ረፍዶብኝ  እንዲህ ሳደርግ መሽቶብኝ ነው የሚሉ ሰንካላ ሰበቦች ውስጥ ራሱን ለመደበቅ የሚሞክር የሆነ እንደሆነ መዘዙ ኦሮምያን አልፎ አገሪትዋ ወደ ሚያካልል ችግር ላለማደጉ ምንም ዐይነት ዋስትና የለም፡፡ ምክንያቱ ኦሮምያ የተነሳውን አለመረጋጋት ወደ ሌላኛው የአገሪቱ ክፍል ለማዛመት የተደረጉ ጥረቶች እንደነበሩ በጥቂቱም ቢሆን ጎንደርና ጎጃም ማሳያዎች ናቸው፡፡

ሌላው ልብ ሊባልበት የሚገባው ነግር ቢኖር በአዲስ አበባና ፊንፊኔ አካባቢ የኦሮምያ ልዩ ዞን ማስትር ፕላን በተመለከተ መንግሰት በተለያየ መዋቅር ህዝቡን የሚያደናግሩ እርስ በርስ የሚጣረሱ መግለጫዎች ሲያወጣ ሰምተናል ታዝበናል ተደምመናል፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አቶ አባዱላ ገመዳ በዚሁ ጉዳይ ላይ ከኢቢሲ (EBC) ባደረጉት ቆይታ ስለጉዳዩ ሰፋ ያለ ማብራርያ የሰጡ ሲሆን ስለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ አስመልክተውም አያይዘው ሲናገሩ በማስተር ፕላኑ  ላይ ህዝብ እንዲወያይበት ከተደረገ በሃላ ህዝቡ ማስተር ፕላኑ የማይቀበለው የሆነ እንደሆነ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱም ይዘጋል ሲሉ ከቀናት በሀላ የአዲስ አበባ መስተዳድር በተመሳሳይ የሚድያ አውትር ኢቢሲ ማለቴ ነው ባስነገረው መግለጫ የፕሮጀክት

ጽ/ቤቱ ከ 2006 ዓ.ም ጀምሮ ተዘግቷል ብሎናል፡፡ መንግስት ከነዚህ አይነት እርስ በርስ የሚጋጩ መግለጫዎች ምን ለማትረፍ በማሰብ እንደሆነ  እንቆቅልሽ ኖኖብኛል፡፡ ይባስም ብሎ የአዲስ አበባ መስተዳደር በዚሁ መግለጫው እንደነገረን በዚሁ በተዘጋ ጽ/ቤት በህገ ወጥ መንገድ የስራ ቅጥር ማስታወቅያ ሲወጣ እንደነበረና መረጃም እንዳለው ገልጾልናል አድኖ ለህግ እንደሚያቀርባቸው ጭምር ዝቷል፡፡ ይህ ዓይነቱ ድርጊት የመንግስት ዝርክርክነት ማሳያ ከሞሆን አልፎ አስነዋሪ ድርጊትና ቅሌቱን እወቁልኝ ባይ ተራ አድራጎት ነው፡፡ ይህ ሁሉ መግለጫ የሚያወጣው የአዲስ አበባ መስተዳደር ሪፖርትር በታህሣስ 17 ቀን 2008 ዓ.ም እትሙ እንዳስነበበን መስተዳድሩ በ 2006 እና 2007 ዓ.ም ለፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ካፒታል በጀት እንዳጸደቀ ነው፡፡ አሁን ለተነሳው የህዝብ ጥያቄ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በሃሳብ ሆነ በተግባር በመዝጋት ብቻ መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል ሊታወቅ ይገባል፡፡  ምክንያቱ የፕሮጀክጥ ጽ/ቤቱ እግረ መንገድ የተጠቀሰ ጉዳይ እንጂ የዋናው አጀንዳ አንኳር አይደለም፡፡

**የኦሮምያ ከተሞችን መልሶ ለማቋቋም ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ** ይህ አዋጅ ተፈጻሚነት ወሰኑ ኦሮምያ ክልልን የሚመለከት ሲሆን በተወሰነም መልኩም ቢሆን በጨረፍታ ከማስትር ፕለኑ ጋር ቀጥተኛ ያልሆነ የመመሳሰል ይዘት ይኖሮዋል፡፡ አዋጁ የወጣው በክልሉ ህግ የማውጣት ስልጣን ባለው ምክር ቤት (ጨፌ) ሲሂሆን ይህ ምክር ቤት የሚያወጣቸው ህጎች የተፈጻሚነት ወሰናቸው ክልሉን ብቻ ይመለከታል፡፡ ታህሣስ 17 ቀን 2008 ዓ.ም ለሪፖርትር የኦሮምያ ክልል መንግስት ካቢኔ አባለና የመንግስት ኮሙኒኬስን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ አቶ ፍቃዱ ተሰማ እንደገለጹት አዋጁ አዲስ አዋጅ አለመሆኑን በማስገንዘ የአዋጁን ሁለት መሰረታዊ ቁም ነገሮችን አብራርቷል ፡፡ ሀላፊው ያሉት ሪፖርትር እዳስቀመጠው

> *"አዋጅ ሳይሆን የአዋጅ ማሻሻያ ነው፡፡አዋጁ የወጣው ከ 15 ዓመት በፊት ነው፡፡ ይህንን አዋጅ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ማሻሻል ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ያለችበት ደረጃ ከ ዛሬ 15 ዓመት ባለችበት ደረጃ አይደለም፡፡ ከተሞቻችን የቱሪዝም የኢንቨስትምንትና የንግድ ማእከላት መሆን አለባቸው፡፡ በከተሞች የሚነሮው ህዝብ ትልቅ እድገት አለው፡፡ የከተሞችን እድገት የሚመጥን አዋጅ ማውጣት አስፈጊ ነው፡፡ ህዝቡ የመንገድ የውኃና የኤሌክትሪክ አቅርቦቶችን ይፈልጋል፡፡ የስራ እድልና የጽዳት አቅርቦት አገልግሎቶችን ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ከዚህ በፊት አነዚህን አገልግሎቶች ለማቅረብ ከተሞች የሚያመነጩት ገቢ ወደ ክልል ፈሰስ ያደርጉና ክልል በበጀት መልክ ይመድብላቸው ነበር ነበር፡፡ በዚህ አዋጅም የተደረገው በከተሞቹ ላይ እየተጠየቁ ያሉ የልማት ጥያቄዎች ሰፊና ዘርፈ ብዙ ስለሆኑ ከተማው የሚሰበስበው ገቢ እዝያው መቶ በመቶ እንዲጠቀም የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ የተቀደሰ ሀሳብ ነው፡፡ ከተሞች በጀት ወደ ላይ ልከው የተወሰነ ከሚመደብላቸው ይልቅ ሙሉውን እዚያው እንዲጠቀሙ ማድረግ የተቀደሰ ሀሳብ ነው፡፡ ሁለተኛ ከመልካም አስተዳደር ጋር ተያይዞ በከተሞች ላይ የነበረው አረጃጀት ለአብነት አዳማን ብንወስድ ባለው መዋቅር የከተማ አስተዳደርና የቀበሌ መዋቅር*

*ብቻ ነው የነበረው፡፡ በጣም ሰፊ ለሆነ አዳማ የንግድና የኢንቨስትምነት ከተማ ለሆነው አዳማ የከተማና የቀበሌ መዋቅር ብቻ የመልካም አስተዳደር ችግሩ ሊፈታ አይችልም፡፡ ስለዚ በቀበሌና በከተማ አስተዳደር አንድ መዋቅር እንዲጨመር ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ለምሳሌ ሻሸመኔና ኩየራ እንውሰድ ኩየራ ከዓመታት በፊት ጥያቄ አቅርቦ በሻሸመኔ ስር አንደ ክፍለ ከተማ ሆኖ ተቀላቀለ፡፡ ስለዚ ከተሞቹ ተወያይተው ሲስማሙ የሚያደርጉት ነገር ነው፡፡ በገጠር ያሉ ተጎራባች ከተሞች እየተወያዩ መግባባት ላይ ሲደርሱ የሚፈጥሩት አንድ መዋቅር ነው፡፡ከፈለጉ ይተሳሰራሉ፡፡ ክልፈለጉ ይተውታል፡፡"*

የዚህ አዋጅ ተፈጻሚነት ወሰን ምንም እንኳን በኦሮምያ ክልላዊ መንግስት መሬት ቢሆንም ቅድም በዚሁ ርእስ መግብያየ ላይ እንደገለጽኩት በማስተሳሰር ረገድ ከማስተር ፕላኑ ጋር በመጠኑም ቢሆን ተመሳሳይነት ይኖሮዋል፡፡ ማስትር ፕላኑ አዲስ አበባንና አጎራባች የኦሮምያ ልዩ ዞኖች በልማት ማስተሳሰር ሲሆን የተሻሻለው የኦሮምያ የከተሞች አዋጅ ደግሞ የክልሉ ያደጉ ከተሞችና አጎራባች ከተሞችን በልማትና በአስተዳደር እንደ አስፈላጊነቱ የህዝቡን ፍላጎትና መልካም ፍቃድ መሰራት በማድረግ ማስተሳስር ነው፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት እንደ ሀላፊው አበባል እንደሆነና የአዋጁ መንፈስ በትክክል የገለጹት አይነት የሆነ እንደሆነ በክልልሉ ታላላቅ ከተማች የሚገኙ አጎራባች ከተሞች በክፍለ ከተማ መዋቅር ይቀላቀሉና እንደ ከተማ የመቀጠል ህልውናቸው ያከትማል፡፡ ይህ ዓይነቱ አሰራር በአንድ ክልል ውስጥ የሚፈጸምና የአደረጃጃትና የመዋቅር ለውጥ እንጂ የክልሉን ልአላዊ መሬት ለሌላ ክልል አሳልፎ የመስጠት ጉዳይ ስላልሆን አዋጁ ይህ ነው ሊባል የሚችል ችግር የሚፈጥር ባይሆኑም በዚሁ ጉዳይ በማስተር ፕላኑ ያደረጉት ሰፊ አፍራሽ ዘመቻ ሰሚ ጆሮ ያጡት አፍራሽ ሀይሎችና አንዳድ በስም እንቆረቆርለታለን የሚሉ የኦሮሞ ሊሂቃን ተብየዎች ይህ አዋጅ ቀደም ሲል በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀውን የአዲስ አበባና ፊንፊኔ ዙርያ ኦሮምያ ልዩ ዞኖች ማስተር ፕላን ለማስፈጸም ሆን ተብሎ መልኩን ለውጦ የወጣ አዋጅ ነው በማለት ባሰራጩት ሰፊ ዘመቻ ህዝቡን በብልጠት በማደናገር ሰፊ ውዥምብር ሊፈጠር ችሏል፡፡በዚህ ረገድ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለተው የኦሮምያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ማስተር ፕላኑ ሳይለይለትና ተገቢውን ግልጽነት ሳይፈጥር እንዲሁ ዓይነቱ ህግ ለማውጣት ሲያስብ ጸድቆ ህግ ከመሆኑ በፊት ካለፈው ትምህርት በመውሰድ ሰፊ ማብራርያ መስጠት ሲገባው በቸልተኝነት ሊያልፈው መቻሉ በከፊልም ቢሆን ለተፈጠሩ አሳዛኝ ክስተቶች የድርሻውን ሀላፊነት ሊወስድ ይገባል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ነገሮች ወደ መርገባቸው አቅጣጫ ይዘው ከፍተኛ ሁከትና ግርግር ባስተናገዱት አንዳንድ ከተማዎችም ጭምር የሠላም አየር መተንፈስ ከጀመሩ ቀናቶች ተቆጥረዋል፡፡ በዚህ ሰዓት መንግስት ሰከን ባለአስተሳባብ ለጉዳዩ ከፍተኛ ቱክረት በመስጥት የማረጋጋት ስራ መስራት ብቻ ሳይሆን የውስጠ መረጋገት ስራም ሊከውን ይገባዋል፡፡ ታህሣስ 17 ቀን 2008 ዓ.ም ሪፖርተር በፊት ገጹ፤ ***የኦሮምያ ክልል ከአዲስ አበባ የሚያገኘውን ልዩ ጥቅም የሚያጠና ግብረ ሀይል ተቋቋመ*** በማለት አስነብቦናል፡፡ ለዚህም ዜናው በዋቢነት የጠቀሳቸው የክልሉ ካቢኔ አባልና የመንግስተ ኮሚኒካሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሀላፊ አቶ ፍቃዱ ተሰማን ነው፡፡ ይህ ጉዳይ

በ1987 ዓ.ም የጸደቀው ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 (5) የሚመለከት ሲሆን ከሰሞኑን ትኩሳት ጋር በአንዳንድ ወገኖች ተያይዞ መነሳት መጀመሩ ተከትሎ ትኩረት እያገኙ ከመጡ ጉዳዮች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ግን ቆየት ያለ ፖለቲካዊ ሳይሆን ሕግ መሠረት ያደረገ የቆየ አጀንዳ ነው፡፡ ሕገ መንግስቱ ስራ ላይ ከዋለ 20 ዓመት አልፎታል፡፡ ሕገ መንገስቱ ላይ ዝርዝር ህግ ይወጣላቸዋል ተብለው ከተጠቀሱ ተጨማሪ ዝርዝር ህግ እንዲወጣለቸው ከተጠቀሱ አንቀጾች እስካሁን ዝርዝር ህግ ያልወጣለት ጉዳይ የኦሮምያ ልዩ ጥቅምን በተመለከተ የሚያትተውን ይህ ክፍል  በውል የሚታወቅ ነው፡፡ ስለሆነም አሁን ለተፈጠረው ነገር እንደ ቀጥተኛ ምክንያት እንኳ  ተደርጎ ባይወሰድ በመጠኑም ቢሆን አስተዋጽኦ ማድረጉ አይቀሬ ነው፡፡ ምክንያቱ ማስተር ፕላኑ ኦሮምያ ሊያገኝ ይገባዋል ተብሎ የተደነገገውን ጥቅም ያለውጫዊ ግፊት  በማስቀደም ቢመጣ ኖሮ እንደ ልዩ ጥቅም ትሩፋት የመቆጠር እድል ሊኖሮው ይችል ነበር፡፡

ፖለቲካዊ ጉዳዮች ግብረ ኃይል በማቋቋም መፍትሄ መፈለግ የተለመደ አይነት አሰራር ሲሆን የህግ ጉዳዮች እንደ ፖለቲካ ጉዳይ በኮሚቴ ሆነ በግብረ ኃይል ማስጠናት ለነገሮች አመጣጥ ካለን የተዛባ ምልከታ የሚመነጭ ይመስለኛል፡፡  ሕገ መንግስቱ የወጣው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀጥተኛ ውይይት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አጽዳቂነት ሲሆን ሕገ መንግስቱን ተከትለው የሚወጡ አዋጆች ዝርዝር ህጎች የማውጣት ስልጣኑ በህገ መንስቱ አንቀጽ 55 (1) ላይ እንደተጠቀሰው የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን ሕገ መንግስቱ የመተርጎም ስልጣን ደግሞ የፌደሬሽን ምክር ቤት ነው (አንቀጽ 62(1))፡፡ ስለዚ ሕገ መንግስቱ ተከትለው የሚመጡና የትርጉም ሆነ ተጨማሪ ዝርዝር ሕግ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮት በፌደራል መንግስቱ ስልጣን ስር የሚወድቁ ናቸው ማለት ነው፡፡ ታድያ ይህ ከሆን የኦሮምያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሰት ግብረ ኃይል ማቋቋም ለምን አስፈለገው? ምክንያቱ ከህግ ለመነጨ ጥያቄ ፖሊቲካዊ መፍትሄ ማፈላለግ ተገቢ አይደላም ሳይ ሆን ሕገ መንግሰታዊ ስርአቱን የተከተላ አይደለም ጭምር ነው፡፡ የኦሮምያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ድርሻ ግብረ ኃይል ማቋቋም ሳይሆን በጉዳዩ ላይ ስልጣን ላለው አካል ጥያቄ መቅረብ ነው፡፡ ዝርዝር ሕግ እንዲወጣለት ከኖነ ሕገ መንግስቱን ተከትለው የሚወጡ አዋጆችን የማውጣት ስልጣን ለተሠጠው ለኢፊዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን፡፡ የሕገ መንግሰት ትርጉም የሚያስፈልገው እንደሆነ ደግሞ ለኢፊዴሪ የፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፡፡ ከዚ በዘለለ የሚደረጉ ድርጊቶች ህዝቡን የሚያደናግሩና ወደ ሌላ ረብሻና ብጥብጥ የሚጋብዙ አደገኛ ሁነቶች ናቸው፡፡ምክንያቱ የኦሮምያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አጥንቶ የሚያመጣው ልዩ ጥቅም ጉዳዩ የሚቀርብላቸው የፌደራል ምክር ቤቶች ተቀባይነት ቢያጣስ፡፡ ተገቢነት የለውም ብለው በማመናቸው ብቻ ሳይሆን ጉዳዩ ጥናት እንኳ ያስፈልገዋል ከተባለ በራሳቸው መንገድና ባለሞያዎች አንጂ በኦሮምያ መንገድና ባለሞያ የተጠና ጉዳይ መሰረት በማድረግ ሕግ የማውጣት ግዴታ ስለሌቻው ብቻ ሳይሆን ድርጊቱ በህግ የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር የሚጋፋ በመሆኑ ላይቀበሉት ይችላሉ፡፡ እንደ ግብአት መጠቀም ይቻል ይሆናል፡፡ ነገር ግን የግብረ ሀይሉ ጥናት የቀጥታ ተፈጻሚነት ሊኖሮው አይችልም፡፡ የትኛውንም ክልል አለኝ ብሎ ለሚያስበው በሕገ መንግስቱን መሰረት የሚቀርብ ጉዳይ የፌደራል ጉዳይ እንደመሆኑ መጠን አለኝ የሚለውን ጥቅም ከመጠየቅ ውጪ ለጉዳዩ ግብረ ኃይል የማቋቋም ሆነ የማስጠናት

መብት ሆነ ሀላፊን የለውም፡፡ የክልሎችና የፌደራል ስልጣን በተመለከተ በሕገ መንግስቱ በግልጽ የተቀመጡ በመሆናቸው የስልጣን ወሰን በከሻገር በወቅታዊ ሁኔታዎች ተገፋፍቶ በሌለህ ስልጣን ላይ ግብረ ኃይል ሆነ ከሚቴ ማዋቀር የአገሪትዋን አድነትና ሕገ መንግስታዊ ስርአቱን መፈታተን ነው፡፡ መንግስት ምን ጊዜም መንግስት ነውና ግራቀኙን ይመልከት የሕግ ጉዳዮች በህግ የፖሊቲካ ጉዳዮች በፖሊቲካ መነጽር እንያቸው፡፡ ጊዝያዊ ትኩሳቶችን ለማስታገስ ሲባል መሰረታችንን አንሰርስር፡፡

**በፉፉ ቀጀላ**
**ጥር** 2008 **ዓ.ም**